# ያገር ልጅ ዲያሥፖራ!

ከዓሣዬ

04/28/10

እሥከ መቼ ድረሥ በሃገር ልጅ ጨከነን
የቆምንለትን ሕዝብ ለጠላት ኣጋልጠን
ፍጹም ሣይሰማን ሰብዕናውን እረግጠን
በሥልጡን ከሃዲዎች ከዓላማችን እርቀን
ከወያኔው ወጥመድ ዘው ብለን ገብተን
የኣረናን መድረክ፣ሥዬና ገብሩን ኣቅፈን፣
ላቀዱት ግፍ ሥኬት የገንዘብ ሃይል ሁነን
እንዴት ድጋፍ እንሥጥ?ሃገር እንዲበተን!?

የኢትዮጵያ ሥሟ ከመዝገብ ተፍቆ
በጠባብ ዘረኞች ክልል ተተክቶ
ኢትዮጵያዊ መሆን ከወንጀል ተቆጥሮ፣
ኣረንጓዴ፣ብጫው፣ቀዩ ባንዲራችን
ሕገ ወጥ ተብሎ እንዳይደርሥ ከቤታችን
ከታሪክ መዝገብ ፍቀው፣ኣዋጅ ሲያወጡብን
ቆርጠን ካልተዋጋን እንደ ዜጋ ቆመን
ዲያሥፖራ በታሪክ እንጠየቃለን!
ኋላ ለመጪው ትውልድ፣ምን እንመልሣለን!?

ለሃገር ሟቹን ኣውጋዥ፣ ሆነን ባላጋራ
ለተጧጧፈው ትግል እየሆነን ደንቃራ
ዳግማዊ ወያኔን ሥዬን የምንጠራ
ኣይደል በሕዝባችን
በሁለተኛው ዙር ላይ፣ ልንጭነው መከራ!?
ኧረ ተው ኣይበጅም! እጅ ኣንሥጥ ዲያሥፖራ
በትግል ለመጣል የዘረኛን ሤራ
ተባብረን በመቆም ለሃገር እንሥራ!።

ዘረኛና ፋሺሥት ኣንድ ላይ ኣብረው
በወያኔ ድጋፍ ገንዘብ ተደጉመው
ዛሬም እንደ ትላንት ሠምና ጨርቅ ሆነው
ዲያሥፖራን ለማጥቃት ትከሻ ተደጋግፈው
የኢትዮጵያ ኣዳኟን ልጆቿን ነጣጥለው
ሁለገብ ታጋዩን ለማድከም ከፋፍለው
በፓልቶክ መሥኮት ላይ ያጓራሉ ይኸው
ትግሉን ለመበተን ትዕዛዝ ተቀብለው!።

እኮ እንዴት!
ለወገናችን ገዳይ ዕድሜ ቀጣይ ሆነን
ዳግማዊ ወያኔ፣የስየን ኣረና፣በሕዝቡ ላይ ጭነን
ለትግሉ ጋሬጣ ለምን እንሆናለን!?
ኧረ ተው ኣንሞኝ ፣ ያገር ልጅ ዲያሥፖራ
ወያኔን በመቅበር ሆነን ያገር ኣውራ፣
እሥቲ እናውጣው ሕዝቡን ከኣፋኞች ጭቆና
የወደቁ ታጋዮች፣የዜግነት ግዳጅ፣ ዕዳ ኣለብንና!
ሥለዚህ ዘብ እንቁም ለማይቀረው ሞቱ
ከእንግዲህሥ ይብቃን ትግልን ማጓተቱ!

This document was created with Win2PDF available at http://www.win2pdf.com.
The unregistered version of Win2PDF is for evaluation or non-commercial use only.
This page will not be added after purchasing Win2PDF.